## ከአቶ ስለሺነህ (ከካናዳ) የተላከ እ-ጦማር፡-

ለክቡራት፡እና፡ክቡራን፡የአመሪካ፡ነፋስ፡ድምፅ፡አማርኛው፡ክፍል፡ዜና፡አዘጋጆች፣
ዋሽንግተን፡ዲ፡ሲ፣
የተባበሩት፡አመሪካ፡መንግሥታት፤
በተቀዳሚ፡ጤና፡ይስጥልኝ፡እያልኩ፣ለበዓለ፡ጥምቀቱም፡በሰላም፡እና፡ጤና፡እንዲ፡አደርሳችሁ፡ ከፍ፡ያለ፡ምኞቴን፡እገልጻለሁ።
ዝግጅታችሁን፡በእሚገባ፡እከታተላለሁ።የእንግልጣር፡ቋንቋ፡የተቀየጠበት፡አማርኛ፡አነጋገር፡ ሲገጥማችሁም፡በማረም፡ስታስተካክሉ፡በመስማቴ፡ከልብ፡አመስግኛችኋለሁ።ግዜው፣የአማርኛ፡ ነጥበ፡ሥነ፡ሥርዓትን፡ጭምር፡ሥነ፡ጽሑፋችንን፡እየተፈታተነ፡ባሕላችንንም፡በወጥነት፡ ለማካሄድ፡የተቸገርንበት፡ነው፡ብየ፡አስባለሁ።በዚህ፡ተፈታታኝ፡ወቅትም፡እያሌ፡ሀገር፡ወዳድ፡ ኢትዮጵያውያት/ን፡ሊቀ፡ምሁራንም፡በቁጭት፡ታሪካችንን፡እየመረመሩ፡እንድናውቀው፡በየኅዋ፡ ሰሌዳው፡አሰራጭተውልን፡እናነባለን።ስንቶቻችን፡ትኩረት፡ሰጥተን፡እንደተጠቀምንበት፡ግን፡ በእርግጠኛነት፡መመስከር፡አልችልም።
ሆነና፣ዛሬ፡ለእናንተ፡ለመጻፍ፡ያነሣሣኝ፡ቁም፡ነገር፣በቅርቡ፡ስለ፡ገና፡በዓል፡ለሀገር፡ቤት፡ኗሪ፡ ወገኖቻችንም፡የአደረጋችሁትን፡ቃለ፡መጠይቅ፡እና፡መልሶቻቸውን፡በማገናዘብ፡ነው።እናም፣ የኢትዮጵያን፡ገና፡ማክበር፡የእሚኖርብን፡በመስከረም፡፱፡ቀን፡ነው።ታኅሣሥ፡፱፡ቀንን፡ማሰብ፡ የነበረብን፡ደግሞ፣እመ፡ቤታችን፡ቅድስት፡ማርያም፡የእግዚአብሔር፡ወልድ፡ኢየሱስ፡ክርስቶስን፡ መፅነስ፡መልአኩ፡ቅዱስ፡ገብርኤል፡የምሥራች፡ያላትን፡እና፡ሁለተኛም፡ታኅሣሥ፡፳፡ቀን፡ የፀነሰችበትን፡ዕለት፡ነበረ።
ኢትዮጵያችን፡የመጀመሪያ፡ሰው፡ዘር፡እና፡ግእዝ፡(መጀመሪያ)፡ቋንቋ፡የተፈጠረባት፡የዓለማት፡ በኩር፣ሀገረ፡እግዚአብሔር፡ስለ፡ሆነች፤መዕራባዊያኑ፡ገናን፡ዛፍ፡እያስጌጡ፡አከባበርም፡ከእኛው፡ የገዳ፡ባሕላችን፡የተወረሰ፡ይመስለኛል።

ስለዚህ፣ወደ፡ናዝሬት፡(አዳማ፡)ሄዳችሁ፡ቃለ፡መጠይቅ፡ስታደርጉም፡ለአካባቢው፡እንግዳ፡ ባለመሆኑ፤ድሮ፡በትልቅ፡ዛፍ፡ሥር፡ያደርጉት፡የነበረውን፣ዛሬ፣ቻይናዊ፡ሠራሽ፡ዛፎችን፡እየገዙ፡ እቤታቸው፡በዓሉን፡ቢያከብሩ፡ለእኔ፡የእሚያስደንቀኝ፡አይሆንም።ሌላው፡ትኩረታችሁ፡ደግሞ፣ በምጣኔ፡ሀብት፡ላይ፡ሁኔታ፡ወገኖቻችን፡በዓሉን፡እንዴት፡ሊቋቋሙት፡እንደ፡ቻሉ፡ለማወቅ፡እና፡ የሥነ፡መንግሥታዊውን፡አቋም፡ሊያስገመግም፡በእሚችል፡መሰለኝ።በዚህም፡ምክንያት፣ የወገኖቻችንን፡አኳኋን፡ለዓለማት፡የማስተዋወቃችሁ፡ዘዴ፡የእሚደገፍ፡ነው።ግን፣ገናን፡ ምክንያት፡አድርጋችሁ፡ስለ፡ነበረ፣የኢትዮጵያን፡ባሕል፡እና፡በትክክለኛው፡ወር፡አለመከበሩን፡ እንኳ፡ከአነጋገራችኋቸው፡የቤተ፡ክህነት፡ካህናት፡አለመስማቴ፡ደንቆኛል።ይህ፡በመሆኑ፣ለወደፊቱ፡ ትምህርት፡እንዲሆነን፤የተከበሩ፡ንቡረ፡እድ፡ኤርምያስ፡ከበደ፡ወልደ፡ኢየሱስን፡ፈቃድ፡ ጠይቃችሁ፡እና፡ግዜ፡ካላቸው፡ቃለ፡መጠይቅ፡እንድታደርጉላቸው፡በትሕትና፡አሳስባለሁ።
ክቡር፡ንቡረ፡እድ፡ኤርምያስ፡ከበደ፡ወልደ፡ኢየሱስን፡ለመጠየቅ፥

ኅዋ፡ሰሌዳ፥ www.ekogs.org
እ.ጦማር፥ info@ethkogserv.org

ከወገኖቻችን፡ጋራ፡እንዳንራራቅ፡አገናኝ፡እና፡ዜና፡አቅራቢ፡በመሆናችሁ እኮራባችኋለሁ።የአለፈውን፡ዓመት፡አሠራራችሁን፡በመገምገም፡ለእሚቀጥለው፡ዓመት፡በተሻለ፡ሁኔታ፡ለመሥራት፡ስትወያዩ፡አዳምጬለሁ።ከግል፡ኑሮ፡ጥቅማችሁም፡ባሻገር፡ለሀገር፡እና፡ወገን፡ለእሚጠቅሙ፡ትኩረት፡ስለ፡ሰጣችሁ፡ለኣርኣያነታችሁ፡እሰዬው፡አሰኝታችሁኛል።እናም፡እግዚአብሔር፡ለዚያ፡አድርሶን፡በሰላም፡እና፡ጤና፡ሐሣባችሁን፡ለማከናወን፡ያብቃችሁ።እኔንም፡ለማዳመጥ፡ያብቃኝ።

ኢትዮጵያ፡ለዘላለም፡ትኑር።አሜን።
አክባሪ፡ኢትዮጵያዊው፡ወገናችሁ፣
ስለሺ፡ነህ፡ገላነህ፣ካናዳ።
እ.ጦማር፥ sileshineh@yahoo.com
ስልክ፡ቁጥር፥ ፮፻፲፬-፯፻፴፫-፮ሺ፯፻፰

## ለዚህ፡ ለአቶ ስለሺ ገላነህ የእ-ጦማር አባሪ ደብዳቤ የተሰጠ መልስ፡-

ለአመሪካ ድምፅ ነፉስ ድምፅ የጻፉት ደብዳቤ፡ የሚደነቅ ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ ይህን ያስደረገዎ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትዎ ስለኾነ፡ እውነተኛ ማንነትዎን፡ ለእኛ ብቻ ሳይኾን፡ ለሌላውም አረጋግጠዋል። በዚሁ ማንነትዎ፡ ለፈጸሙት፡ ለዚህ፡ መልካም አገልግሎትዎ፡ ለ"ታማኝ አገልጋዩ"፡ ከሙገሳ ጋር፡ በጎ ዋጋውን የከፈለ ጌታ፡ ለእርስዎም፡ እንዲህ፡ እንደሚያደርግ በማመን፡ ለዚህ ቸርነቱ እናመሰግነዋለን።

ኹላችንም፡ በያለንበት፡ ይህን የመሰለውን በጎ ምግባር በመፈጸም፡ የተልእኮ ግዳጃችንን እንድንቀጥልበት ይኹን!